ትንሣኤሽን ያሳየን

ውዲቷ ኢትዮጵያ

ሀገረ እግዚአብሔር

ትንሣኤሽን ያሳየን

ውዲቷ ኢትዮጵያ

ሀገረ እግዚአብሔር

ትንሣኤሽን ያሳየን

ውዲቷ ኢትዮጵያ

ሀገረ እግዚአብሔር



ትንሣኤሽን ያሳየን ውዲቷ ኢትዮጵያ ሀገረ እግዚአብሔር

https://t.me/EthiopeTowoderos

https://fb.me/EthiopeTewoderos

ትንሣኤሽን ያሳየን ውዲቷ ኢትዮጵያ ሀገረ እግዚአብሔር

ትንሣኤሽን ያሳየን ውዲቷ ኢትዮጵያ ሀገረ እግዚአብሔር

"ትንቢትን አትናቁ ፤ ሁሉን ፈትኑ መልካሙንም ያዙ"

ለጥያቄዎቻችሁ መልስ

ሰላም እንዴት ናችሁ ውድ የኢትዮጵያ ልጆች ?

ሁላችሁም ማለትም በውስጥ መስመር ጥያቄ የጠየቃችሁኝና ያልጠየቃችሁኝም እንዲሁ እስከ መጨረሻው ይህንን ጹሁፍ በትእግስት አንብቡት ።

ሣልሣዊ ቴዎድሮስ ማነው ?

የኢትዮጵያ ትንሣኤ መቼ ነው ?

ኢትዮጵያ የአለም ብርሃን

ኢትዮጵያ የአለም ብርሃን ምዘገባው እውነተኛ ነው ወይስ ሀሰተኛ ?

አባ ዘወንጌል ማን ናቸው ?

ምን አጥፍተን ነው መቅሰፍት የሚመጣብን ?

ስለ ጳጳሳቱና ሰለ መምሕራኖች ፥ መምሕር ዘበነ ለማ ንግግር https://youtu.be/DoCpkuqyi-4

መልካም ንባብ !!!

<u>ማሳሰቢያ</u>

ከዚህ በታች ያሉት ጹሁፎች የግል ማለትም የራሴ ምልከታና ሃሳብ ነውና ስህተት ብሳሳት በውስጥ መስመር ማረም ትችላላችሁ።

ትንሣኤሽን ያሳየን ውዲቷ ኢትዮጵያ ሀገረ እግዜብሔር

<u>ሣልሣዊ ቴዎድሮስ ማነው ?</u>

ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ድርሳናትን ፥ ገድላትን እንዲሁም መጽሀፍ ቅዱስን ማገላበጥ ይኖርብናል ። በተለይም የገብረ መስቀል አየነው መልእክት ለዚህ መልስ ይሆነናል ። ⁅ የገ/መስቀል አየነው መልእክት - https://t.me/EthiopeTowoderos/2050 ⁆ ስለዚህም ከዚያ መልእክት እየወሰድኩ እጽፍላችኋለሁ ማለት ነው ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ስለ ሳልሳዊ ቴዎደሮስ በተለያየ መፅሃፍ ሰፍሮ ይገኛል፡፡
ማስረጃዎች

1- **ፍካሬ ኢየሱስ**
ፋካሬ ኢየሱስ ላይ ደግሞ “ታሪካዊ እና ደገኛ ንጉስ ይነግሳል በዚያን ጊዜ የአንድ ላም ወተት የአንድ በሬ እሸት ይበቃል” ይላል፡፡
"ከዚህ በኋላ በምስራቅ: በኩል: ታሪካዊና: ደገኛ: የሆነ: ንጉሥ: ይነሳል፤ እሱም: ፈቃዴን: የፈፀሙትን: ከመከራ: ያተረፍኳቸውን: የሚሰበስብ: ነው" ፍካሬ ኢየሱስ

(ፍካሬ ኢየሱስ = https://t.me/EthiopeTowoderos/1350)

2- **ራእዩ ለአቡነ ሲኖዳ**
አቡነ ሲኖዳ ባየውና በጻፈው
ራእይ ላይ ስለዚኽ ነገር በስፋት እንዲኽ ይገልጠዋል፡-
“ወእምድኅረዝ በእሙንቱ መዋዕል ይትነሥኡ ክልኤቱ ነገሥት አሐዱ ንጉሠ
ሮም ዘስሙ “እ” ወአሐዱ ንጉሠ ኢትዮጵያ ዘስሙ “ትዮዳ”... ” (ከዚኽ በኋላ
በዚያ ዘመን ኹለት ነገሥታት ይነሣሉ፤ አንዱ ስሙ “እ” ተብሎ የሚጠራ የሮም
ንጉሥ ነው፤ አንደኛውም “ትዮዳ” የሚባል የኢትዮጵያ ንጉሥ ነው። ከሊቃ
ጳጳሶቻቸው፤ ከሰራዊቶቻቸው፤ ከሕዝብ ኹሉ ጋርም በኢየሩሳሌም ይሰበሰባሉ፤
ሃይማኖትን እያቀኑ በዚያ ለሰባት ወር ይቀመጣሉ፤ ያን ጊዜ በየቋንቋው የእኛ
ሃይማኖት ይሻላል እያሉ ክርክር ሙግት ይኾናል። ከዚኽ በኋላ የእስክንድርያው
ሊቀ ጳጳሳት ተነሥቶ በጉባኤው ኹሉ ፊት “እግዚአብሔር በጥንተ ተፈጥሮ
የፈጠራችኁ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው ብቸኛ ልጁን በማመን የጠራችኁ ወገኖች
ስሙኝ፤ በዛሬው ዕለት ግሩምና ቅዱስ ራእይን ተመለከትኁ። ነገር ግን ያየኹትን
ራእይ አልናገርም፤ የሚያምነኝ የለምና፤ ነገር ግን ወደ ጎልጎታ ሰዎችን ላኩ፤
ከጌታችን መቃብር መሬትን (ዐፈርን) አምጡ፤ በቤተ ክርስቲያን ውስጥም
እነሰንሳለኁ፤ የእኛ የሚኾን ቅዳሴን በአንድ ወገን እንቀድስ፤ የሮሜ ሊቀ ጳጳሳት
በሌላኛው ወገን ቅዳሴን ያድርግ፤ ሰዎች ኹሉ እየተመለከቱት ከእኛ በአንዱ ላይ
ከሰማይ ተአምር የኾነ ከዚኽ በኋላ በዚያ ሃይማኖት በአንድ ላይ እንተባበር፤
ሕዝቡም ኹሉ በዚያ ሃይማኖት አንድ እንኾናለን ይበሉ” ይላል።

3 – ገድለ ፊቅጦር
ሰማዕቱ ቅዱስ ፊቅጦር አንድ የሚነገር ትልቅ ታሪክ አለው፡፡ እርሱም በሰማዕትነት ካረፈ ከብዙ ዘመን በኋላ በራእይ ተገልጦ በ8ኛው ሺህ ዘመን በሀገራችን በኢትዮጵያና በግብፅ እንዲሁም በቁስጥንጥንያና በሮም ወደፊት የሚሆነውን ነገር ሁሉ በግልጽ የተናገረ መሆኑ ነው፡፡ ‹‹ስለ ሃይማኖት ቅዱስ ፊቅጦር ያየው ራእይ›› የሚል መጠሪያ ያለው ይህ ራእይ በሀገራችን ጎጃም ደብረ ጽሞና ገዳም ውስጥ ይገኛል፡፡ ይህንን በተመለከተ ቅዱስ ፊቅጦር የተናገረውንና ቅዱስ ገድሉ ላይ የተጻፈውን ቀጥሎ እንመለከተዋለን፡-
‹‹...በእስላሞችም ጊዜ በግብፅ ሀገር ሁሉ የክርስቶስ ሕማ አይቋረጥም፡፡ የጾም፣ የጸሎትና የቍርባን እምነት ይኖራል፡፡ ከእስላሞች ጋር እየኖሩ የሃይማኖት ጽናት ትበዛለች፤ በማርቆስ መንበርም የሊቀ ጳጳሳት መሾምም አይቋረጥም፤ በሊቀ ጳጳሳት እጅ በየደረጃው የጳጳሳት፣ የኤጲስ ቆጶሳት፣ የቀሳውስትና የዲያቆናት ሹመትም አይቋረጥም፡፡ የእስላሞችም መንግሥት ጥቂት ዘመናት ናቸው፡፡ ከጥቂት ዘመናት በኋላ እግዚአብሔር በኢትዮጵያ ሀገር ክርስቶስን የሚወድ ቅዱስ ሰው ያነግሣል፡፡ ዐረማውያንም በእርሱ እጅ ይደመሰሳሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ወደ ግብፅ ሀገር ሄዶ እስላሞችንና መንግሥታቸውን ሁሉ ያጠፋል፡፡ እግዚአብሔር በቍስጥንጥንያ እርሱን የሚወድ ስሙ ትውልደ አንበሳ የተባለ ሰው ያነግሳል፡፡ ከኢትዮጵያ ንጉሥ ጋር ይገናኝ ዘንድ ይመጣል፡፡ በግብፅ መሀል ቦታ ላይ ይገናኛሉ፡፡ ከእርሱ ጋርም የእስክንድሪያ ሊቀ ጳጳሳትና የቍስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳሳት ይገናኛሉ፡፡ የኢትዮጵያ ንጉሥ ሠራዊቱን በደቡብ በኩል ትቶ የቍስጥንጥንያም ንጉሥ ሠራዊቱን በሰሜን በኩል ትቶ ሁለቱ ነገሥታትና ሁለቱ ሊቃነ ጳጳሳት ተገናኝተው እርስ በእርሳቸው ሰላምታ ይሰጣጣሉ፤ ሊቃነ ጳጳሳቶቹ በመንበራቸው ላይ ተቀምጠው ነገሥታቱን ‹በየመንበራችሁ ላይ ተቀመጡ› ይሏቸዋል፡፡ የቍስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳሳት ‹የእኛ ሃይማኖት ትበልጣለች› ይላል፡፡ የእስክንድሪያውም ሊቀ ጳጳሳት ‹እግዚአብሔር የሰጠኝን ቃል እኔ እነግራችኋለሁ› ይላል፡፡ ሁለቱ ነገሥታትም ‹አባታችን በል ንገረን› ይሉታል፡፡ ‹የአባ ሲኖዳ ወደምትሆን ወደዚህች ታላቅ ቤተክርስቲያን ገብተን በእንዲት

ታቦት ላይ እኔ እቀድሳለሁ፣ ይህ ባልደረባዬ ሊቀ ጳጳሳት በአንዲቷ ታቦት ላይ ይቀድስ፤ ሁሉም ሕዝብ ሠራዊቶቻችሁም መጥተው ይመልከቱ› ይላል፡፡ ‹መንፈስ ቅዱስ እያያችሁት ከሁለታችን በአንዱ ቁርባን ላይ ከወረደ በዚያ ሃይማኖት ሁላችን እንሂድ፣ ሃይማኖቷም ትታወቃለች ቀንታለችና› ይላቸዋል፡፡ ሁለቱ ነገሥታት ‹እሺ በዚህ ቃል ተስማምተናል፣ የእግዚአብሔር ምክር ናትና› ይሉታል፡፡ ያን ጊዜ ሁለቱ ነገሥታትና ሊቃነ ጳጳሳት ሠራዊቶቻቸውም ሁሉ ካህናቶቻቸውም፣ ሕዝቡም ወደዚህች ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ይገባሉ፡፡ ሁለቱ ሊቃነ ጳጳሳትም በሁለቱ ታቦታት ላይ ይቀድሳሉ፡፡ በዚያ ያሉ ሁሉ እያዩ መንፈስ ቅዱስ በነጭ ርግብ አምሳል ከብርሃን ጋር የእስክንድሪያው ሊቀ ጳጳሳት በቀደሰው ቍርባን ላይ ይወርዳል፡፡ ያን ጊዜ የኢትዮጵያ ንጉሥ ይደሰታል፣ የእርሱም ሊቀ ጳጳሳት ነውና፡፡ በእግዚአብሔር ፊትም የእርሱ የሃይማኖት ሕግ የተወደደ ይሆናል፡፡ የሮም ንጉሥ ግን ከሕዝቦቹ ጋራ ያዝናል፡፡ መጻሕፍቶቻቸውን ሁሉ ሰብስበው ወደ ባሕር ይወረውሯቸዋል፡፡ ሃይማኖታቸውንም ስለአጠፋና መናፍቃን ስላደረጋቸው የቀድሞውን ሊቀ ጳጳሳቸውን ሊዎንን ይረግሙታል፡፡ ሁሉም ወደ አንዲት የእስክንድሪያ ሊቀ ጳጳሳትና የኢትዮጵያ ንጉሥ ሃይማኖት ይመለሳሉ፡፡ ሮምም፣ ግብፅም፣ ኢትዮጵያም ሁሉም የተስማሙ ይሆናሉ፤ በመካከላቸውም ጽኑ ፍቅር ይሆናል፡፡ ሁሉም ሃሌ ሉያ እያሉ እግዚአብሔርን ፈጽመው ያመሰግኑታል፡፡ የኢትዮጵያ ንጉሥና የሮም ንጉሥ እርስ በእርሳቸው እጅ መንሻንና ሰላምታን ተሰጣጥተው ወደየ ሀገራቸው ይመለሳሉ፡፡ ቅዱስ ፊቅጦርም ለእናቱ የሚነግራትን ይህንን ሁሉ ትንቢት ከጨረሰ በኋላ ‹እናቴ ማርታ ሆይ ሰላም ላንቺ ይሁን› ብሎ ከእርሷ ተሰወረ፡፡››

4 - ድርሳነ ኡራኤል

28 ፤ ከሰባት ፡ ሽህ ፡ ዓመት በኋላ ፡(በ1500 ዓ.ም/በ7000 ዓ.ዓ-በስምንተኛው ሽህ) በዓለም ፡ ላይ ፡ ሰላምና ፡ ደስታ ፡ ይታጣል ፤ በመጨረሻውም ፡፡ የአረማውያን ፡ ዘመን ፡ በመሆኑ ፡ ፍቅር ፡ በየጊዜው ፡ እየነደለ ፡ ይሄዳል ፡፡

....

29 ፤ ከመነኮሳት ፡ ማኅበር ፡ ሆነ ፡ ከካህናት ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶችም ፡ በመልካም ፡ ሥራ ፡ አይሄዱም ፡ ጻድቃን ፡ ይመስላሉ ፡ በውስጣቸው ፡ ግን ፡ ተንኮለኞችና ፡ ሐሰተኞች ሴሰኞችም ፡ ናቸው ፡፡

39 ፤ ዳግመኛም ፡ መጋቢት ፡ ሃያ ፡ ዘጠኝ ፡ ቀን ፡ ጥቂቶች ፡ የከዋክብት ፡ ምልክቶች ፡ በሰማይ ፡ ይታያሉ ፡፡

….

41 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የአረማውያን ፡ ዘመን ፡ ያልቅና ፡ የስሙ ፡ ምክክት ፡ < ና > ተብሎ ፡ ከተመለከተው ፡ ንጉሥ ፡ የተወለዱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ያሸንፏቸዋል ፡፡

42 ፤ ከሰብዓ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ሁለት ፡ ከዋክብት ፡ ከፀሐይ ፡ መውጫ ፡ ወጥተው ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ደም ፡ በቀደሰኳት

፡ ቅድስት ሀገር ፡ በሆነች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ይቆማሉ ፡፡

43 ፤ በነዚሁ ፡ ዓመታት ፡ በዚችው ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ በአመዳዩ ፡ ዘመን ፡ የተሸሸጉ ፡ ቅዱሳኖች ፡ ሁሉ ፡ ይሰበሰባሉ ፡፡

44 ፤ አመድ ፡ ከዘነመ ፡ ከአራት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰማዕት ፡ የሆነ ፡ በፊቅጦር ፡ በገድሉ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደተነገረው

፡ የስሙ ፡ ምልክት ፡ < ቴ > ተብሎ ፡ የተመለከተው ፡ ይነግሳል ፡፡

(ቴ - ቴዎድሮስ / ትዮዳ ሣልሣዊ)

49 ፤ በዚያን ፡ ዘመን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥና ፡ በዓለም ፡ ሁሉ ሰላምና

ደስታ ፡ ጥጋብና ፡ ፍጹም ፡ ተድላ ፡ ይሆናል ፡፡ { https://t.me/EthiopeTowoderos/858 }

5 - ራእየ ሳቤላ

"በምስራቅ ባለች ታላቅ ሀገር በርሷ ላይ ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት ጦርነት ይነሳል፣ ከጥቂት ሰወች በስተቀር በርሷ የሚተርፍ የለም።" ራዕየ ሳቤላ

"የአንበሳ: ልጅ: ከምስራቅ: ይመጣል፣ በዚያ: ዘመን: ምድር: ላይ: የፈረሱ: ሀገሮች: ይታነፃሉ፣ ታቦት: ትተከላለች፣ በዓለሙ: ሁሉ: በዘመኑ: ጥጋብ: ይሆናል". . . ራዕየ ሳቤላ

ስለ መከራው ዘመንና ኢትዮጵያ ትንሣኤ አናምንም መጽሀፍ ቅዱስን ብቻ እንቀበላለን ለምትሉ አዋቂ ነን ባይ ሰዎች ደግሞ ይሄው ማስረጃ

ለሁሉም አጥፊዎች፡ ለእያንዳንዱ ቀሳፊ መላክም ሆነ አጥፊ ሰውም ሆነ የሰይጣን አበጋዞች በየቤቱ ደጅ ስለመዘጋጀቱ- ርሱም እያንዳንዳቸውን የሚያጠፉ መሳሪያን በእጃቸው ይዘው ከተማይቱን የሚቀስፉ ይቅረቡ ብሎ በታላቅ ድምፅ በጉሮየ ጮኸ፡፡ ህዝ 9፥1

-የበጉ የደም ማህተም በግንባራቸው ያለባቸውን መቅሰፍቱ እንደማይነካቸው - እግዚያብሄርም በከተማይቱ በእየሩሳሌም መካከል እለፍ በመካከሏም ስለተሰራው ርኩሰት ሁሉ በሚያለቅሱና በሚተክዙ ሰዎች ግንባር ላይ ምልክት ፃፍ አለው፡፡ ህዝ 9፥4

-እኔም እየሰማሁ ለሌላወቹ እርሱን ተከትላችሁ በከተማይቱ መካከል እለፉ ግደሉም አይናችሁ አይራራ አትዘኑም፡፡ ህዝ ምእ 9፥5

-ፅዳቱ ከቤቱ አገልጋዮችና ከአለም ቆነጃጅት ስለመጀመሩ- ሽማግሌውንና ጎበዙን ቆነጃጅቶችንም፤ህፃናቶችንና ሴቶችን ፈፅማችሁ ግደሉ ነገር ግን ምልክቱ ወዳለበት ሰው ሁሉ አትቅረቡ በመቅደሴም ጀምሩ አላቸው፡፡በቤቱም አንፃር ባሉ ሽማግሌዎች ጀመሩ፡፡ ህዝ 9፥6

-ሃጢያተኞች አህዛብን በካህናትና በተወደደች ቤቱ ላይ ስለማሰልጠኑ (የሚረከሰው ቤት የተቀደሰ አይደለምን ርኩሰማ መቼም እርኩስ ነው) -ርሱም ቤቱን አርክሱ በተገደሉትም ሰዎች አደባባዮችን ሙሉ ዉጡ አላቸው እነርሱም ወጥተው በከተማይቱ ገደሉ፡፡ ህዝ 9፥7

ጊዜው መጥቷል ቀኑ ቀርቧል መዓት በብዙዎች ሁሉ ላይ ነውና የሚገዛ ደስ አይበለው የሚሸጥም አያልቅስ፡፡ ህዝ 7፥12

ሰይፍ በውጭ ቸነፈርና ራብ በውስጥ አለ፤በሜዳ ያለው በሰይፍ ይሞታል፤በከተማም ያለውን ቸነፈርና ራብ ይፈጁታል፡፡ ህዝ 7፥15

ከእነርሱም የሚሸሹ ይድናሉ በተራራም ላይ ይሆናሉ፡፡እኔም በሀጢያታቸው ሁሉን እገድላለሁ፡፡ ህዝ7፥16

ለአመፀኛይቱና ለረከሰች ለአስጨናቂቱም ከተማ ወዮላት! ሶፎ 3፥1

ድምፅን አልሰማችም ተግሳፅንም አልተቀበለችም በእግዚያብሄርም አልታመነችም ወደ አምላኳም አልቀረበችም፡፡ ሶፎ 3፥2

በውስጧ ያሉ አለቆቿ እንድሚያገሱ አንበሶች ናቸው ፈራጆቿም እስከ ነገ ድረስ ምንም እንደማያስቀሩ እንደ ማታ ተኩላዎች ናቸው፡፡ ሶፎ 3፥3

በመካከልሽም የዋህና ትሁት ህዝብ አስቀራለሁ በእግዚያብሄርም ስም ይታመናሉ፡፡ ሶፎ 3፥12

ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ የሚማልዱኝ የተበተኑት ሴቶች ልጆቼ ቁርባኔን ያመጡልኛል፡፡ ሶፎ 3፥10

እጃቸውን ለክፋት ያነሳሉ አለቃውና ፈራጁ ጉቦን ይፈልጋሉ፤ትልቁም ሰው እንደ ነፍሱ ምኞት ይናገራል፤እንድሁም ክፋትን ይጎነጉናሉ፡፡ሚክያ 7፥3

ከእነርሱም ሁሉ የተሻለው አርሱ እንደ አሜካላ ነው፤ከሁሉም ቅን የሆነው እንደ ጉርጎችት ነው፤ጠባቆችህ የሚጎበኙበት ቀን መጥቷል፤አሁን ይሸበራሉ፤:ሚክ 7፥4

ወንድ ልጅ አባቱን ይንቃልና፤ሴት ልጅ በእናቷ ላይ ምራቷም በአማቷ ላይ ትነሳለችና የሰው ጠላቶች የቤቱ ሰዎች ናቸውና፡፡ሚክ 7፥5

የምድርንም ከተሞች አጠፋለሁ ምሽጎችህንም ሁሉ አፈርሳለሁ፡፡ ሚክ 5፥11

መተትንም ከእጅህ አጠፋለሁ ሟርተኞችም ከእንግድህ ወድህ አይሆኑልህም፡፡ሚክ 5፥12 በተባረከው ጊዜ ጠንቋይ የለ፤አስጠንቋይ የለ፤ጣኦት ማምለክ የለ..... አሁን አፈዝ

የተቀረፁትን ምስሎችህን ሃውልቶችህን ከመካከልህ አጠፋለሁ ለእጅህም ስራ ከእንግድህ ወድህ አትሰግድም፡፡ ሚክ 5፥13

የማምለኪያ አፀዶችህንም ከመካከልህ እነቅላለሁ ከተሞችህንም አፈርሳለሁ፡፡ ሚክ 5፥15

ባልሰሙም አህዛብ ላይ በቁጣና በመዓት እበቀላለሁ፡፡ ሚክ 5፥15

የእግዚያብሄር ቀን ቀርቧልና ለቀኑ ወዮ! እርሱም ሁሉን ከሚችል ከአምላክ ዘንድ እንደ ጥፋት ይመጣል፡፡ ኢዮኤል 1፥15

መንግስትም ግዛትም ከሰማይ ሁሉ በታች ያሉ የመንግስት ታላቅነት ለልዑል ቅዱሳን ህዝብ ይሰጣል መንግስቱም የዘላለም መንግስት ነው ግዛቶችም ሁሉ ይገዙለታል ፤ ይታዘዙለትማል፡፡ ትንቢተ ዳንኤል 7፥27 = የቴዎድሮስ ዘመን

ከምስራቅ የሚመጣው ሳልሳዊ ቴዎድሮስ ስለመሆኑ-ስድስተኛውም ፅዋውን በታላቁ ወንዝ በኤፍራጥስ ላይ አፈሰሰው ከፀሃይም መውጫ ለሚመጡ ነገስታት መንገድ እንድሰናዳላቸው ውሃው ደረቀ፡፡ራእ 16፥12 ከምስራቅ የሚመጣው ማን ነው? ፀሀየ ፅድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ በመንገዱ ዉሃ ያግደው ይሆን ዳግም ምፅት የምትሉት? ደግሞስ ይህን ካለ በኋላ በምድር ላይ እንደገና ስለምን ስለ ሽህ አመት አወራ? ይህ ለእኔ ምንም ጥያቄ የለውም ግን እናንተን አሁንም እጠይቃችኋለሁ፡፡

የአርማጌዶን ጦርነት (ሶስተኛው የአለም ጦርነት) በቅርቡ ቅዱስ ሳልሳዊ ቴዎድሮስ ሳይወጣ የሚጀምርና ፍፃሜውም በእሱ በቅዱሱ ፍርድ በሚሆነው በዚህ ጦርነት ባለራእዩ ምን ይላል? በእብራይስጥም አርማጌዶን ወደሚባል ስፍራ አስከተቷቸው፡፡ ራእ16፥16

ይህ ትንሳኤ ከመምጣቱ በፊት በሳልሳዊ ቴዎድሮስና በሌሎች መንፈሳዊያን እንድሁም በኢጋንንትና በተላላኪዎቹ የሰው ልጆች መካከል በሚደረግ መንፈሳዊ ውጊያ ሊቃነ መላእክትንና ሁሉንም 99ኙን ነገደ መላእክት ያሳተፈፈው ጦርነት የእግዚያብሄር ጦርነት ስለመባሉ፡፡

ምልክት እያደረጉ የኢጋንንት መናፍስት ናቸውና፤በታላቁም ሁሉን በሚገዛ በእግዚያብሄር ቀን ወደ ሚሆነው ጦር እንድያስከትቷቸው ወደ አለም ሁሉ ነገስታት ይወጣሉ፡፡ራእ 16፥14 ይህ ጦርነት አሁን እየተደረገ ያለ ቢሆንም በዋናነት ግን በዳግም ምፅዓት የሚታይ ይሆናል፡፡

መብረቅና ድምፅም ነጎድጓድም ሆነ፤ትልቅም የምድር መናወጥ ሆነ ሰው በምድር ከተፈጠረ ጀምሮ እንድህ ያለ ታላቅ መናወጥ ከቶ አልነበረም ከሁሉ በለጠ፡፡ ራእ 16፥18

ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ አለም እንደገና ስለመቀጠሏና ምፅዓትም ገና ስለመሆኑ-ታላቂቱም ከተማ በሶስት ተከፋፈለች የአህዛብም ከተማዎች ወደቁ፡፡ታላቂቱም ባቢሎን (አሜሪካ) የብርቱ ቁጣው ወይን ጠጅ የሞላበት ፅዋ እንድሰጣት በእግዚያብሄር ፊት ታሰበች፡፡ ራእ 16፥19

አህዛብም ሁሉ ከዝሙቱዋ ቁጣ ወይን ጠጅ የተነሳ ወድቀዋልና የምድርም ነገስታት ከእርሷ ጋር ሴሰኑ የምድርም ነጋደዎች ከቅምጥልነቷ ሃይል የተነሳ ባለጠጋዎች ሆኑ ብሎ ጮኸ፡፡ራእ 18፥3 ስለውድቀቷም በሩቅ ሆነው እንደሚያለቅሱላት.....

ይህን ሁሉ ካለ በኋላ በምእራፍ 19፥1 ጀምሮ ከዚህ በኋላ ብሎ ይጀምራል.....ምን ማለቱ ነው?ምፅዓት ከሆነ ከዚህ በኋላ ሰው በምድር ላይ ሊይኖርም ለምን ሌላ ታሪክ ቀጠለ?ምን ብሎ መሉውን አንብቡት?ካለ በኋላ ሽህ አመት አለረው ወደ ጥልቅም ጣለው አህዛብንም ወደፊት እንዳያስት ሽህ አመት እስኪፈፀም ድረስ በእርሱ ላይ ዘግቶ ማህተም አደረገበት፡ከዚህም በኋላ ለጥቂት ጊዜ ይፈታ ዘንድ ይገባዋል፡፡ራእ 20፥3 ትርጉም፤ይህ ሽህ አመት የተባለ ጊዜ የቴዎድሮስ ዘመን ሲሆን ለልጀ ልጅ የሚቆይ አስተዳደር ነው፡፡ቢሆንም ሽህ አመት የሚያክል ምቾትና ፅድቅ ለማለት ነው እንጅ 1000 ዓመት የሚቆይ አይደለም፡፡ሄኖክና እዝራ እንዳሉ ምድሪቱንስ ከ8000 እንዳታልፍ ልዑል ገደባት ተብሎ እንደተነገረ፡፡

የማይቀረው ታላቁ ምፃት ከመምጣቱ በፊት ያለው ይህ ትንሳኤ በምድር ላይ ለሽህ አመት በዳኝነት ሰልጣን የሚኖሩ አሉ፤በሂደቱም ሰማእት የሚሆኑ አሉ፤እንደሚከተለው እንድህ ተባለለት፡፡

አረ ሌላም ማስረጃ አለ

መጽሀፈ ሄኖክ መጀምሪያው አካባቢ

መጽሀፈ ኪዳን

ትንቢተ ናሆም 3 ፥ 13

ትንቢተ ህዝቅኤል 30 ፥ 4

ትንቢተ እንባቆም 3 ፥ 7

ትንቢተ ሶፎንያስ 2 ፥ 12

ትንቢተ አሞጽ 3 ፥ 2-8

መጽሀፈ ምሳሌ 8 ፥ 10

መዝሙረ ዳዊት 36 ፥ 17

ትንቢተ ኢሳያስ 5 ፥ 20

ራእየ ዮሐንስ 13

ራእየ ዮሐንስ 20

እነዚህ ከዘመናችን ጋር የሚገናኙ የመጽሀፍ ቅዱስ ትንቢቶችና ቃሎች ናቸው ።

የመጀመሪያው ጥያቄ የተመለሰላችሁ ይመስለኛል ።

ትንሣኤሽን ያሳየን ውዲቷ ኢትዮጵያ ሀገረ እግዚአብሔር

<u>የኢትዮጵያ ትንሣኤ መቼ ነው ?</u>

ርስተ ድንግል ቅድስት ሀገራችን ኢትዮጵያ ብርሃን ፥ ትንሣኤ አላት ካልን መቼ ነው ትንሣኤዋ ፥ በምንስ ምክንያት ትነሣለች ?

"በምስራቅ ባለች ታላቅ ሀገር በርሷ ላይ ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት ጦርነት ይነሳል፣ ከጥቂት ሰወች በስተቀር በርሷ የሚተርፍ የለም።" ራዕየ ሳቤላ

ይህንን የነብይት ሳቤላ ትንቢት አስተውላችሁ አንብቡት ።

ሶስት ቀናን ሶስት ሌሊት በሚሆነው ጦርነት ብቻ ብዙ ሰዎች በኢትዮጵያ እንደሚያልቁ የሚገልጽ ይመስለኛል ።

ኢትዮጵያ ኢይልም እኮ ብትሉኝ እኔ እንደ ግሌ መጽሀፍ ቅዱስ ላይ ምስራቅ እየተባለች የምትጠራው የኛይቱ ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ እንደሆነች አምናለሁ።

ሰብአ ሰገሎች ኢትዮጵያዊ ነበሩ ፥ አስራ ሁለቱም ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ነገስታት እንደነበሩ ታሪክ ይነግረናል ። የአስራ ሁለቱም ነገስታት ስማቸው በታሪክ ተዘግቦ ይገኛል ።

ታድያ መጽሀፍ ቅዱስ ሰብአ ሰገል ከየት ነው የተነሱ የሚለው ? ከምስራቅ ።

ነቢይት ሳቤላም በምስራቅ ባለች ታላቅ ሀገር ብላ የጠራቻት የኛይቱ ሀገር ኢትዮጵያን እንደሆነች አምናለሁ ።

<u>መንግስትን ተሳደቡ ፥ ጳጳሳቱን አንቋሸሹ እያላችሁ የምታሚቸው ጅግናው የተዋህዶ አርበኛ ፥ የድንግልና የልኡል ባሪያ አባ አምኃ ኢየሱስም ለዚህ ህዝብ ብለው ባስተላለፉት የቅዱሳኑ መልክት ላይ ስለ ሚመጣው አስከፊ መከራ ተናግረዋል ።</u>

<u>በመጀመሪያ ግን ተግሳጽንና ስድብን ለይታችሁ እወቁ !!!</u>

ይህ ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት የተባለው መከራ ከሀጢአታችን ባላመመለሳችን ወደ 3 አመት መከራ እንደተቀየረ እገምታለሁ ።

አባቶች ፥ የንብረ መስቀል አየነው መልእክት ላይ ሶስት አመት መከራ እንደሚሆን ተነግሮናል ።

ነገር ግን ጊዜው ሊያጥር ወይንም ሊረዝም የሚችለው ማንኛውም ውሉደ አዳም የሆነ በሙሉ በቀጥተኛዋ ሃይማኖት ጸንቶ ፥ በንስሃ እራሱን አጽድቶ ፥ ከፈጣሪው ቢታረቅ ይህ ግዜ እንደሚያጥርልን ምንም አጠራጠሪ ነገር አይደለም ።

ጠረጋው ከዚያም በኋላ ትንሣኤው ከፊታችን እንደሆነ አባ አምኃ ኢየሱስ ፥ ገብረ መስቀል አየነው ፥ ኢትዮጵያ የአለም ብርሃን መልእክታት ይህንን በደንብ አድርገው ያስረዱናል ።

ስለዚህ በአጠቃላይ ጊዜው ከፊታችን ፥ ቅርብ መሆኑን ባውቅም ከዚህ እስከዚ ዘመን መከራ ይሆናል በዚህ ዘመን ንጉሡ ይመጣል የሚለውን ነገር አላምንበትም ። ምክንያቱም እንደ ሰዎች በንስሃ መመለስ ሊለያይ ይችላል ።

ከእኛ የሚጠበቀው ግን የተለያዩ የመናፍቆች እምነቶችን በመተው ፥ የተለያዩ አሳሳች እምነቶችን ባለመከተል ፥ የአለማቱ ጌታ ፥ አልፋና አሜጋ ፥ ፊተኛውና ኋላኛው ፥ እልፍ አእላፋት ተቆጥሮ የማያልቅ ህቡእ ስሞች ያሉት አንድ አምላክ እግዚአብሔር በደሙ የመሰረታትን አንዲት ቀጥተኛ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን በመከተል ፥ ንስሃ በመግባት ተዘጋጅተን መጠበቅ የኛ ኃላፊነት ነው ።

ትንሣኤሽን ያሳየን ውዲቷ ኢትዮጵያ ሀገረ እግዚአብሔር

ኢትዮጵያ የአለም ብርሃን

ኢትዮጵያ የአለም ብርሃን ፥ ኢትዮጵያ የአለሙ ገዢ መልእክታት እውነተኛ ናቸው ወይንስ ሀሰተኛ ?

ኢትዮጵያ የአለም ብርሃን ሁሉንም መልእክታት እስከአሁን ባላዳምጥም ፥ ባላነብም ። እስከ መልእክት ሶስት ያለውን ግን አዳምጫለሁ ፥ አንብቢያለሁ ።

መልእክታቱ ፍጹም እውነተኛ ፣ ከሀሰተኛ ሰው ሀሳብ የማይወጡ መሆናቸውን ሳነብና ሳዳምጥ ተገንዝቢያለው ።

እና ይህንን የእግዚአብሔር መልእክታት የምታንቋሸሹ ሰዎች ካላችሁ ችግሩ ከመልእክታቱ እንዳልሆነ ልመሰክር እወዳለሁ ፥ ሰባኪ ነን ፥ ዶክተር መምሕር እየተባሉ የሚጠሩት ይህንን መልእክት ምንም ሳያነቡና (ሀሰተኞችን ነው ያልኩ) ሳያዳምጡ እንዲሁ በደፈናው አትመኑ ፣ ሰላም ነው ፣ እግዚአብሔር መሃሪ ነው ፥ ቴዎድሮስ አሁን አይመጣም . . . እያላችሁ የምትመጻደቁ እባካችሁን ወደ ድንግልና ወደ ልኡል ተመለሱ ብየ እለምናችኋለው ።

ትንሣኤሽን ያሳየን ውዲቷ ኢትዮጵያ ሀገረ እግዚአብሔር

<u>ኢትዮጵያ የአለም ብርሃን ምዝገባው እውነተኛ ነው ወይስ ሀሰተኛ ?</u>

ለዚህ ጥያቄ በእኔ የ15 አመት ታዳጊ መንፈሳዊ ብቃት አንጻር ምንም እውነቱ ይህ ነው ብየ ልገልጽላችሁ አይቻለኝም ።

ራእየ ዮሐንስ 20 የቴሌግራም ገጽ ወደላይ ሂጂ መቼ እንደተከፈተ ለማየት ሞክሬ ነበር እና የዚህን መረጃ ባላገኝም እንዲህ የሚል ጀምሮ ያለውን የግሩፑ ጹሁፍና መረጃዎች ተመልክቻለሁ ።

24 April 2019
Biruk converted a basic group to this supergroup «ራእይ ዮሐንስ 20»

ከዚህ ቀን በኋላ ያለው መረጃ ይገኛል ቻናሉ መቼ እንደተከፈተ ግን አላውቅም ።

አንዳንድ የተደለቱ ጹሁፎች እንዳሉም ከ replay ላይ ተገንዝቤያለሁ ።

ለማንኛውም ስለዚህ ምዝገባ እኔ የምላችሁ ነገር አንድ ነገር ብቻ ነው ። እኔ ማንንም አልነቅፍም የግል አስተያየቴ ነው።

በመጀመሪያ እኔ ምዝገባው ተመዝግቤ ነበር ፥ በኋላ ላይ ግን በተመዘገብኩበት መሰረት ተሰርዣያለሁ ።

መልእክታቱ እውነተኛና በቅርቡ ተፈጻሚዎች እንደሆኑ አምናለሁ ፣ ነገር ግን እኒህ መልእክታትን መጠቀሚያ ሊሆኑ ይችላሉ ብየ አስባለሁ ።

የመልእክታቱ አስተላላፊና መዝጋቢዎች ማለትም በተለያዩ መገናኛ ብዙሃኖች ተመዝገቡ የምትሉ አንድ ያልተረዳችሁት ነገር ያለ ይመስለኛል ፥ እርሱም ይህ ሕዝብ ለማያውቀው ሰው የግል አድራሻውን ምን ማስተማመኛ ነገር ኑሮት ነው አሳልፎ የሚሰጠው ።

እስቲ በዚህ ህዝብ ሁናችሁ አንዴ ነገሩን ካልተመለከታችሁት ተመልከቱት ፥ በዚህ በስምንተኛው ሺህ ሰውን ማመን ከባድ የሆነበት ደረጃ ላይ ነን ያለነው ።

እኔ በበኩሌ ምዝገባውን አልተቀበልኩም ።

ስለዚህ ጉዳይ ግን ራእየ ዮሐንስ 20 ግሩፕና ቻናል ያልተመዘገበ ከመከራው አይተርፍም አላሉም ።

እኔ እስከተረዳሁት ከሆነ ተመዝጋቢዎች ጸሎት እንደሚደረግላቸው የተናገሩ መዝጋቢዎች አሉ ።

ከሁሉም በላይ ግን በተዋሕዶ ሃይማኖት እንጽና ።

ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል ሳጥናኤል እኔ ነኝ የፈጠርኋችሁ ባለ ጊዜ አምላካችንን እስከናገኘው ድረስ ባለንበት እንጽና እንዳለ እኛም እንዲሁ እውነትን እስከናገኛት ድረስ በትክክለኛዋ መንገድ እንጽና እላለሁ ።

አባ ዘወንጌል ማን ናቸው ?

ቅዱስ አባ ዘወንጌል- ዘኢትዮጵያ
❊❊❊❊❊❊❊❊❊❊❊❊❊❊❊❊❊❊❊
እንደ እነዚህ ያሉ አባቶች በኢትዮጵያ ይኖራሉ ይላል መጽሐፈ-ሸራቶኤል ።
አባ ዘወንጌል ትግራይ በኢሮብ ወረዳ በአሲምባ ተራራ ይኖሩ ነበር።
እድሜያቸው በግልጽ አይታወቅም ።
ግራ እጃቸው እንደ ፀሐይ ያበራል።
አንዳንዴ ሽማግሌ መስለው ይታያሉ ፥ አንዳንዴ ወጣት መስለው ይታያሉ።
ሲፈልጉ ይሰወራሉ ፥ ሲፈልጉ ይገለጻሉ።
እስከ 20 ዓመታት ተሰውረው ይገለጻሉ።
ከንፍ አውጥተው እንደ ወፍ በረው ይሄዳሉ።
የነገውን መከራና ትንሳኤ ይናገራሉ ፥ ስለ ራሳቸው ምንም አይናገሩም።
ግንኙነታቸው ከሰውራን አባቶችና እናቶች ጋር ነው።
መስከረም 19 2012 ዓም የመስቀለ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን
ሰርተው አጠናቀዋል ፥ ንጉሱ ቴዎድሮስ የሚያርፍበት ቤተክርስቲያን መሆኑን ተናግረዋል።

በዚህ አመት ብቻ ብዙ ቅዱሳን አባቶቻችንን አጥተናል ፥ ‘ ጌታ ሆይ! የኢትዮጵያን መከራ ከምታሳየን ነፍሳችንን ወደ አንተ ውሰዳት’ እያሉ የጸለዩም ይመስላል ።

የኢትዮጵያ ትንሣኤ ቅርብ እንደሆነ አንዱ ማረጋገጫችንም የአሲምባው ቅዱስ አባ ዘወንጌል ናቸው ።

አባ ዘወንጌል በዘመነ ዮሐንስ ጥቅምት 10 ቀን 2012ዓ.ም ከ2፡20 ሰዓት ላይ አርፈዋል። በረከታቸው ይደርብን !!!

ከአባ ዘወንጌል ዜና እረፍት በኋላ የኢትዮጵያ የምጥ ጊዜ እየተባባሰ የጀመረው እርሳቸው ባረፉ በነገራው ነበር ፥ ይሄውም የአሮሞው ፍጅት ነበር ።

አንዳንድ አፈ ጻድቅ የሆኑ ሰባኪ ነን ባዮች የአባ ዘወንጌልን ትንቢት ሲያናንቁና ሲያጣጥሉ በጆሮየ ሰምቻለሁ ፥ በአይኔም አይቻለሁ ።

ነገር ግን አስታውሉ ህይ ተረት አይደለም ፥ የአሲምባው ቅዱስ አባ ዘወንጌል የኢትዮጵያን ትንሣኤ መድረሱን ነግረውን አርፈዋል ፥ በኋላ አልሰማንም እንዳንል ንስሃ እንግባ ።

አሁንም በድጋሚ በረከታቸው ይደርብን ! ! !

አባቶች 7 ሰባት ታላላቅ ገዳማት እንደሚቃጠሉ ነግረውናል ፥ አሁንም በንግርቱ መሰረት ከጥፋት መንገዳችን ካልተመለስን ለንስሃ ጊዜ የማይሰጥ ፥ 12 ሰአታት ብቻ የሚሰጥ ክፉ ገዳይ በሽታ ይመጣል ፥ የዚህ በሽታም መድሃኒቱ ያለው አንድ አምላክ እግዚአብሔር ጋር ብቻ ነው ።

❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊

ትንሣኤሽን ያሳየን ውዲቷ ኢትዮጵያ ሀገረ እግዚአብሔር

ምን አጥፍተን ነው መቅሰፍት የሚመጣብን ?

ይህንን ጥያቄ የጠየቃችሁኝ እያወቃችሁ ይሁን አይሁን አላውቅም ፥ ምክንያቱም ይህ ለማንም ያልተሰወረ ነገር ነው ። አሁንም የጠየቅሽኝ እኅቴ ይህንን እያነበብሽው ይሆናልና መልሱ ይሄው ፡ -

አንደኛውና የመጀመሪያው የፈጣሪን ቁጣ የሚያመጣው አስርቱ ትእዛዛትን መጣስና ማፍረስ ነው ። እስቲ እናስተውል ከአስርቱ ትእዛዛተ እግዚአብሔር ውስጥ በዚህ ዘመን ትውልድ ላይ ያልተጣሰ ህግ አለን ?

እውነትን የሚናገር ፋራ እየተባለ መሳቂያ ይሆናል። ይሄን እግዚአብሄር ይፈቅዳልን ?

ኹለተኛው ከተፈጥሮ ህግ መውጣት ነው ።

እነዚህም ግብረ ሰዶማውያን የተባሉት ናቸው ።

ፈጣሪያችን ለአዳም ሔዋንን ፈጠረ እንጅ ለአዳም አዳምን ለሔዋን ሔዋንን አልፈጠረም ፥ እነዚህ ሰዎች የተፈጥሮን ህግ በመጻረር የሴትን ማኅጸን በወንድ ውስጥ በመክተት ፥ ወንድና ወንድ በመዳራት ፥ ሴትና ሴት በመዳራት የልኡልን ቁጣ የሚያመጣ የተጠላ የሰይጣን ስራ እየፈጸሙ ይገኛሉ ፥ ይልቁንም ሰለጠኑ በምትሏቸው ሀገራት ይህ እንደ መብት ህግ ወጥቶለታል ።

የቫቲካኑ ጳጳስ ተበየ አባ ፍራንሲስ {አቡነ ማለት አባታችን ማለት ነውና አቡነ አልለውም።}

በቤተክርስቲያን ሰዶማውያንን ሲድሩ ታይተዋል ።

ይህ ግብረ ሰዶማውያን አሁን ላይ ኢይናቸውን ወደ ኢትዮጵያ አዙረዋል ፥ ቅድስት ምድር ኢትዮጵያ የ 7 ኪዳናት ሀብት ያላል ምድር ስለሆነች ይህ ነገር በዚች ምድር ከተፈጸመ አምላክን እንደሚያስቆጣው የታወቀ ነገር ነው ።

ባለፈው በአዲስ አበባው ጁፒተር ሆቴል ሰዶማውያን ምን ተወያይተው እንደነበር አንድ አምላክ ብቻ ነው የሚያውቀው ፥ ከዚህ አስከፊ ሀጢአት አምላካችን ይሰውረን ነው እንጅ ሌላ ምንም አይባልም ።

በዚህ ሃጢአት ላይ የወደቅን ሰዎች ካለን ደግሞ እራሳችንን በንስሃ እናንጻ።

ሊላኛው ሃጢአት ደግሞ ያልሆኑትን ልሁን ፥ እውነተኛዋን ባሕልን መርሳት ፥ ማንነትን በመጣል በመንጋ በማሰብ የውጮችን እምነት ፣ ሃሳብ ፣ ትምሕርት ልውረስ የሚያስብል እራስን የሚያስንቅ ሃሳብ ነው ።

ኣስቲ አስታውሱ ሴቶችና ወንዶች ፥ አባቶችና እናቶች ይህ ትንቢት በዚህ ትውልድ ላይ አልተፈጸመም ፡ -

" ባህላቸውን : ይለውጣሉ ፣ የያዙትን : ይጥላሉ ፣ ያላዩትን : ይናፍቃሉ ፣ ሰብአዊ : ባህሪያቸውን : በእንስሳ : ባህርይ : ይለውጣሉ ፣ ነውርን : ይንቃሉ ፣ ኃፍረታቸውን : ይገልጣሉ. . . እግዚአብሔር : ኃጢያታቸውን : ስለታገሳቸው : እንደሌለ : ይቆጥሩታል ፣ በስራቸው : የጎሰቆሉ : በሀሳባቸው : የረከሱ : ናቸው። " ፍካሬ ኢየሱስ

ምንም ጥርጥር የለውም ፥ ይህ ትንቢት ሙሉ ለሙሉ በእኛ በአሁኑ ትውልድ ላይ ተፈጽሟል ።

የኢትዮጵያን ሃይማኖት አርቶዶክስ ተዋሕዶን ትተን ተሃድሶ {ፕሮቴስታንት} ፥ ቅባት ፥ ጸጋ ፥ ደቂቀ ኤልያስ ፥ ምንፍቅና {የውጭን መናፈቅ} እነዚህን የጥፋት መንገዶች እየተከተልን ነው ያለነው ።

ሴቶች ከህጻንነታቸው ጀምሮ ቆንጆ ነሽ ፥ ቆንጆ ናት ፥ ስታምር እየተባሉ ነው ያደጉት ። እውነት የሰው ልጅ በውጫዊ ውበት ይለካልን ?

ሴቶችና ወንዶች የተፈጥሮ ጸጉራቸውን ትተው በአርቴፊሻል መቀየይ ይሄ እውነት ከእግዚአብሄር ዘንድ ነው ?

ሴቶች አሁንማ ወንዶችም ጀምረዋል < ጥፍር ቀለም መቀባት > እውነት ይሄ ነገር መነሻው ከማን ነው ?

ጥፍር እኮ የራሱ የተፈጥሮ ውበት አለው ይሄውም የአዳም አባታችንና የሔዋን እናታችን ልብስ እንደነበረ ይነገራል ።

እና ይህ አግባብ ነው ?

ሴቶች እኅቶቼ አስተሳሰባችሁ በውጮች ታጥቧል{ እውነተኛ የተዋሕዶ ልጆችን አላልኩም }

አይን መኳል ፥ ቅንድብ መሸለል ፥ እንሶስላ መሞቅ ፥ የሌጌዎን ቅባትን ከንፈር ላይ መቀባት . . . አረ ስንቱን ልጥቀሰው እኒህ ሁሉ በአሁኑ ትውልድ ላይ ይታያሉ ። እንዲያውም ይህንን ያላደረገ እንደማይገባው አላዋቂ አድርጎ ይቆጠራል ።

እናቶቻችን እኮ ድሮ እንሶስላን የሚሞቁት በከንቱ ለማጌጥ አይደለም ፥ እንሶስላ ለቁርጥማት መድሃኒት ስለሚሆን ነው ።

ለስሙ ሁሉም አምላክ ከፈቀደ ይላሉ ፥ የእግዚአብሄርን ስም በከንቱ አትጥራ የሚለው እኮ ገና ከዚህ ነው የሚጣሰው ።

መጽሐፈ ሄኖክ ምእራፍ 2 ቁጥር ቁጥር 18 ጀምራችሁ ብታነቡ ይህ በእግዚአብሄር ዘንድ የተጠላ እንደሆነ ትገነዘባላችሁ ፥ ይህንንም ካልሰማችሁ ግን ልኡል ይራራላችሁ ነው እንጂ ሌላ ምንም አልላችሁም ።

ይሄውም የወደቁት መላእክት ማለትም ደቂቀ ሴቶች ያመጡት ርኩሰት ነው ።

ዝሙት = ይህ ሃጢአትም ከተለመደ ቆይቷል ፥ እንዲኑም ይህንን ያላደረገ ሰው ፋራ ሙድ የሚይገባው እየተባለ ይሰደባል ። እስከዚህም ድረስ ሰይጣን አመለካከታችንን አጥቦታል ።

ኦሪት ዘዳግም ምእራፍ 22 ቁጥር 5 ላይ የተጻፈው የፈጣሪ ህግ እንዲህ ይላል ።



ይህማ አንድያውን የተገረሰሰ የፈጣሪ ህግ ነው ። አይደለም እንዴ ? ዋሸሁ ?

በህገራችን በተለይም ከቅርብ ጊዜ በኋላ በህገራችን የአውሬው ስራ አስፈጻሚ የሆኑ የሮከና ፥ የዝሙት ፥ የሀጢአት ሳቅ . . .

የተቀላቀለባቸው የሀጢአት ዘፈኖች በዝተዋል ።

ዘፈን ኹሉ ሃጢአት አይደለም ፥ ነገር ግን የዝሙትና የሃጢአት ዘፈን ሃጢአት ነው ።

ስለ ህገርና ስለ ማንነት የተዘፈኑት ዘፈኖች ግን ሃጢአት አይደለም።

< ኢትዮጵያ ለዘለአለም ትሳቅ > የሚል ትውልድ ላይ ነው ያለነው ፥ እውነት ይሄ በጣም ያሳዝናል ።

በኖኅ ዘመን ይሰሩ የነበሩ ሃጢአቶች በላይ በአሁኑ ዘመን ይሰራል ፥ እና ከዚህ በላይ ልኡልን የሚያስቆጣ ምን ሃጢአት አለ ።

ከእግዚአብሔር ቃሎች በላይ የዝሙትና የከንቱ ደስታ ዘፈኖች በአንድ ቀን ውስጥ ብዙ ሽህ ሰው አፍ ውስጥ ይገባሉ ።

እውነት ልኡል እግዚአብሔር መንገዳቸውን ወደ እርሱ መንገድ ይምራልን ፥ ይምራን !!!

ትንሣኤሽን ያሳየን ውዲቷ ኢትዮጵያ ሀገረ እግዚአብሔር

ስለ ጳጳሳቱና ሰለ መምሕራኖች ፥ መምሕር ዶ/ር ዘበነ ለማ ንግግር ፤

{https://youtu.be/DoCpkuqyi-4}

ድርሳነ ዑራኤል ዘጥቅምት ሁለተኛ ምዕራፍ

29 ፤ ከመነኮሳት ፡ ማኅበር ፡ ሆነ ፡ ከካህናት ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶችም ፡ በመልካም ፡ ሥራ ፡ አይሄዱም ፡ ጻድቃን ፡ ይመስላሉ ፡ በውስጣቸው ፡ ግን ፡ ተንኮለኞችና ፡ ሐሰተኞች ፡ ሴሰኞችም ፡ ናቸው ።።

ይህ ቃል የተነገረው ለአሁኑ ዘመን{ እውነተኞችን አይጨምርም } ጳጳሳት ፥ ካሕናት ፥ ሰባኪያን ተብየዎች የተነገረ ነው ።

" በዚያን ጊዜ: ለብዙ: ክብር: የታጩ: በማዕርግ: በሹመት: ያደጉ: በከፍተኛ: ደረጃ: ላይ: የሚገኙ: ሁሉ: አደራቸውን: ይዘነጋሉ፣ ሀገራቸውን: ይከዳሉ፣ መሀላቸውን: ያፈርሳሉ፣ ከባለሟልነታቸው: ይወጣሉ፣ ከማዕርግና: ሹመት: ጓደኞቻቸው: ይለያሉ". . ."ባለስልጣኖች: ከአመፀኞች: ጋር: ይተባበራሉ:". . ."ከፉ: ስራቸው: በተገለፀባቸው: ጊዜ: ይፀፀታሉ" ፍካሬ ኢየሱስ

" በዚያን ጊዜ: የምድረበዳ: አውሬዎች: ቦታቸውን: ትተው: ወደከተማ: ይገባሉ። አውሬ: የተባሉ: ባሕታውያን: ናቸው። ባሕታውያን: ነን: ሲሉ: የብትሕናውን: ስራ: አይሰሩም፣ ፆም: ፀሎት: ሌሊት: መንቃት: የለባቸውም". . ."ወንድማቸውን: ባለንጀራቸውን: አይወዱም: እንደ: ዓለማዊ: ሰው: የዚህን: ዓለም: ሹመት: ይሻሉ: " ፍካሬ ኢየሱስ

ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሲያንገላቱትና ሲፈርዱበት የነበሩት እኮ እውነተኛ መሳይ ካሕናቶች ናቸው።

የአሁኑ ዘመን ሰባኪያን ዶክተር መምሕር የተባሉ ፥ አፈ ጻድቅ ፥ እውነትን እያወቁት ለሕይወታቸው ስለሚሰጉ የማይመሰክሩ ፥ ሕዝቡን ሰላም ነው ፥ እግዚአብሔር መሃሪ ነው ፥ ጊዜው ገና ነው ቴዎድሮስ አሁን አይመጣም ፥ ገና ምን ታየና እያሉ ሕዝቡን የሚያዘናጉ ሰዎች እንዳሉ ሁሉም ያውቀዋል ።

ጳጳሳቱ { ከሀቀኞቹ በስተቀር } የመንግሥት ስራ አስፈጻሚዎች ነው እንጂ ጳጳሳት አይመስሉም።

የልኡል እውነተኛና የታመኑ ባሪያዎች ግን እነርሱ አይደሉም ፥ ከሰው ተብልለው ፥ ራሳቸውን አዋርደው ፥ ምድራዊ ክብርን ንቀው ፥ በየነዳናው ለማኝ መስለው የሚታዩት እነርሱ እውነተኞቹ የተውሕዶ መሪዎች ናቸው።

አባ አምኃ ኢየሱስ እውነትን ስለመሰከሩ አይደለም እንዴ ያ ሁሉ ምድራዊ መከራ የደረሰባቸው ?

አቡነ ጴጥሮስ የዛኔ ዝም ብለው ማለፍ አይችሉም ነበር ? ነገር ግን በምድራዊ ፈተና ሰማያዊ ጸጋ እንደሚሰጥ ስላመኑ ገዝተው አረፉ ።

ስለዚህ ልኡል እግዚአብሔር ለአስመሳዮቹ ጳጳሳትና ሰዎች በሙሉ ማስተዋልን ይስጥልን !!!

ነገር ግን አስታውሱ ጸሐዩ ጳጳስ የሚመጣበት ጊዜና ተዋሕዶ የምትነግስበት ጌዜ ሩቅ አይሆንም ።

<u>የመምሕር ዶ/ር ዘበነ ለማ ንግግር ፤ { https://youtu.be/DoCpkuqyi-4 }</u>

የሐሰተኞች ነቢያትና ባሕታውያን አካሄድ - ከ900 በላይ ሰዎች በምቱበት ታሪክ ሲመዘን - በመምህር ዶ/ር ዘበነ ለማ

በዚህ ቪዲዮ ላይ ጊዜው ገና እንደሆነና ንጉሡ ቴዎድሮስ በቅርቡ እንደማይመጣ እርግጠኛ ሁኖ ገልጿል።

ከዚህ በፊት ገብረ መስቀል አየነው መልእክት ላይ < <u>...የቤተ ክርስቲያንን አባቶችን ምን አደነዘዛቸው? ></u>

በሚለው ርእስ ላይ የገለጸው ነገር በቂ ስለሆነ እርሱን እንደወረደ አስቀምጣለሁ ።

መቼም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባቶቻችን በአሁኑ ሰዓት ፓውዝ(ያስቆማቸው)

ያደረጋቸው ነገር ባይታወቅም ከመናፍቃን ሰዎች ጋር የሚመሳሰሉበት አንደኛው ነገር ስም አወጣጣቸው ነው::ስምን መላክ ያወጣዋል የሚለው ድሮ ስለሆነ::አሁን ሊቀ ጠበብት፤ሊቀ ሃዋርያ፤መጋቢ ሚስጥር፤ሊቀ ሊቃውንት .....ይባባላሉ::ይህ ነገር ድሮም አለ የድሮወቹ ግን አሁን የሉም::በእውነት ይህ ነገር በህይዎት ካልኖሩበት ሸክም ነው::እኔ ይህን ነገር በመፃፌ እኔ ማን ነኝ ብዮ እራሴን እጠይቃለሁ ነገር ግን የእውነት ፈራጅ ህሊናየ ቃሉ ትክክል ነው ይለኛል::አንተ ግን ይህን መናገር አትችልም አትመጥንም ይለኛል::አዎ በምፅፈው ነገር ሁሉ እኔ ሆኜ ስላልተገኘው አልመጥንም::ሃጢያትን እንደተራራ ተሸክሜ ይህን እናገር ዘንድ አይገባኝም::ግን በህይዎቴ

የምቀናበት፤ የተደበቀ እውነት እንዳለ ደግሞ ነፍሴ ፍፁም ታምናለች::ይህን ደግሞ እስከ መጨረሻው የመመስከር የስላሴ ግደታ አለብኝ::አሁንም እደግመዋለሁ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን አብዛሃኛዎቹ መምህራን ለትንሳኤው ስላልተፃፉ ስለትንሳኤው መስማት፤መናገርም ሆነ ሲነገር መስማት አይፈልጉም::አንዳንዶቹም ደንገጥ እንኳን አይሉም::ጊዜው ገና ነው ይሉሃል::ይህን እኛ አንደርስበትም፤ገና እስላም ይገዛል.....ወዘተ ይላሉ::በእውነት ያልተፈፀሙ ነገሮችን እስኪ ንገሩኝ፤ያልታዩ ምልክቶችስ ይኖሩ ይሆን::ወዳጅ ይልቅ የትንሳኤውን ሰባኪዎች ታያቸዋለህ እነሱ እንዳንተ ባማረ ልብስና ስም የተሸለሙ እንዳይመስሉህ እሳት እየተፉ ይመጡልሃል::እነሱ አሁን የተናቁ ናቸው፤ለእግራቸው ጫማ ለሰውነታቸው እዚህ ግባ የሚባል ልብስ የላቸውም፤ሰውነታቸው የተጎሳቆለ ነው::ምግባቸውም ብልይሚልን ማመስገን ነው::እነሱ ታናናሽ ናቸው ከአንተ በጣም የሚያንሱ ግን የስላሴን እውነት እንደ ውሃ ይግቱሀል::የእምነት ልዕልናን ገንዘብ ያደረጉ፤አዕምሮ ፅኑአን ናቸው::
ተስፋቸው፤ሃብታቸው፤እውቀታቸው፤ዉበታቸው፤ሰላማቸው ሁሉ እሱ እግዚያብሄር ነው::
አንተ ግን ቅስናን ከዶክትሬትህ እያጣቀስክ እንጀራህን ታበስላለህ::መድሃኒያለምን ከምታገኘውና እኔ ዶክተር ነኝ ከምትል የትኛው እንደሚያስደስትህ አንተ ታውቃለህ::ደግሞም የማትወልደው ልጅ አለህ(ቦርጭ አልከው:ያን ቀጣፊ እንደሻንጣ ከፊትህ ተሸክመህ እየሄድክ) መስቀሉንስ የሌጊዎን ቅባት ከንፈሪን ተቀብታ ሱሪ ለብሳ ስትመጣ ለምን አሳለምካት?እኔ ከመድሃኒያለም በልጬ አጠይቅህ ዘንድ አይቻለኝም እንጅ ብዙ የምናወራው ነበር::አሁን አንተ እንኳን ህዝብ ልታስተምር ለራስህም አልሆንክ፤ሀገርህና ሃይማኖትህ እንኳን ወደ የት እየሄዱ እንደሆነ ለማወቅ ደንዝዘሃል::የተኛው አንበሳ ሆይ ንቃ::እንደ ዮሃንስ መጥምቅ መምህር ወመገስፅ ስትሆን ነው ሃይልህ ከአንተ ጋር የሚሆነው::ያለዚያ እንደሶምሶን ጠላቶች ጠላቶችህ ይበረቱብሃል::በደል አለ ብትበድልም እንደ ጴጥሮስ አልቅስ እሱ ይቅር ባይ ነው::ደግሞስ ካልደፈረስ ይጠራልን አጥፍተህ ደካማነትህን አይተህ ስትመለስ የእሱ ሁሉን ቻይነት ይጎላብሃል::እየፈራህና እየተንቀጠቀጥክ ታመልከዋለህ::በፊትህ ያዘልከውን ጣልና ሁሉን ትተው እንደተከተሉት እንደ አባቶችህ ሃዋሪያት ሁን::ተከለሃይማኖት እግሩን ናቃት አንተ ትርፍ ስጋ ፍለጋ ትሄዳለህ ? ከመጣብህም አጥፋው::ዊ በእውነት ይህ ትውልድ እጅግ አስጨናቂ ትውልድ ነው፤ይህ ትውልድ በእሳት የሚጫወት ትውልድ ነው፤እኔም አብሬ ከዚህ ትውልድ ጋር በእሳት የምጫወት ትውልድ ነኝ::
እንጃ በድፍረት በእሳት በመጫዎቴ እግዚያብሄር ይቅር ይለኝ ይሆን? አባቶቼ ሆይ እኔ አሁን ይህን የምላችሁ ከእናንተ በላይ አውቄ አይደለም ግን <u>የተዘጋጀ ሰይፍና ሽጉጥ በእናንተ ላይ ያለ ይመስለኛል::ልጆቻችሁም እናንተን አጥተው መቃብር ላይ ሄደው እናንተን ፍቱን ማለት የለባቸውም::::</u>

ይህ ሙሉ መልስ ይሆናል ብየ አስባለሁ ።

ነገር ግን ጌዜው ገና ነው እያሉ ቢያሞኟችሁ እንዳትሰሙ ነቅታችሁ ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ ፥ ገና ነው ብላችሁ የምታስቡ ካላችሁ ደግሞ ሳታስቡት ከፊታችሁ መሆኑን ስታውቁ እንዳትደነግጡ አሁን ነገርኳችሁ ።

ወንድም ተክለኪዳን ለዚህ ምላሽ ሰጥቶ ነበር { https://www.facebook.com/100003662512341/posts/1973466869452044/?app=fbl } ይህ ነው ምላሹ።

እኔ በግሌ ይህ ምላሽ ትክክል ነው አላስብም ።

እንደዚህ አይነት ሰው መሆንክን ስለተረዳውና ስለተነገረኝ ማለት አስፈላጊ አይደለም ።

መምሕር ዘበነ ለማ የሚያስተላልፋቸው መልእክታትና ትምሕርቶች ለማንኛውም ሰው ደስ የሚልና ውስጥ ድረስ የሚገቡ ናቸው ፥ ነገር ግን ባለፈው ጊዜው ገና ነው በማለታቸው ሰው ናቸውና አጥፍተው ሊሆን ይችላል ብሎ ማለፍ ተገቢ ነው ብየ አስባለሁ ።

ትንሣኤሽን ያሳየን ውዲቷ ኢትዮጵያ ሀገረ እግዜብሔር

አጠቃላይ መፍትሔው ምንድር ነው ?

መፍትሔው አንድ ብቻ ነው እርሱም

1ኛ - በቀጥተኛዋና በትክክለኛዋ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት መጽናት

2ኛ - ንስሃ መግባት

3 - ተዘጋጅቶ መጠበቅ

እኒህን ካደረግን በልኡል ፈቃድ የኢትዮጵያን ትንሣኤ ልናይ እንችላለን ።

ድንግልን ፥ ሰማእታትን ፥ ጻድቃንን ፥ መላእክትን መለመን ፥ መማጸን አለብን ።

የታዘዙት መቅሰፍታት ብዙ ናቸው ሲጠቃለሉ ግን 3 ናቸው ተብሎ ተነግሮናል ፥ እኒህን መቅሰፍታት ባናልፍ ራሱ እኛ ከኢትዮጵያ ትንሣኤ በላይ የምንናፍቃት መንግስተ ሰማያትን እንዳናጣት እንጸልይ ፥ ካልጸለይን ምድራዊ ሞት ሳይሆን የሞት ሞት እንሞታለንና አደራ ።

“ ያንጊዜ አለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዛሬ ያልተደረገ፥ ከእንግዲም ወዲያ የማይደረግ ታላቅ መከርራ ይሆናል።እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ኖሮ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር ፣ ነገር ግን ስለ ተመረጡት እነዚያ ቀኖች ያጥራሉ። ”

የማቴዎስ ወንጌል ምእራፍ 24 ፥ 21

የኢትዮጵያን ትንሣኤ ለማየት ያብቃን !!!

ተጻፈ ከእናንተ በእድሜ ባነሰው በሃጢአት ግን በበለጠው ወንድማችሁ ሚኪዶኤል

በ ሰኔ 4 / 2012 አመተ ምሕረት ከቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ

ለአስተያየት ፥ ለተግሳጽ ለሁሉም ነገር

tewoderos3rd@gmail.com

https://t.me/Tewoderos3rd

http://m.me/EthiopeTewoderos

ከነዚህ ባንዱ መላክ ትችላላችሁ ።

ትንሣኤሽን ያሳየን ውዲቷ ኢትዮጵያ ሀገረ እግዚአብሔር